Abrham Yohanes https://chilot.me

የኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

# የአዋጅ ቁጥር 251/1993 ማሻሻያ ረቂቅ አጭር ማብራሪያ

# የአዋጅ ቁጥር 251/1993 ማሻሻያ ረቂቅ አጭር ማብራሪያ

## 1. መግቢያ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62፣ 48፣83 እና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/93 መሠረት ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም፣ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብቶችን በተመለከተ በሕገ መንግሥቱ መሠረት የመወሰን፣ የሕዝቦችን የእኩልነት መብት እና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር የማድረግ፣ በክልሎች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን የመፍታት፣ ፍትሃዊ የድጎማ እና የጋራ ገቢዎች ክፍፍል እንዲኖር የማድረግ፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር አስፈላጊ የሆኑ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን የመለየት፣ ማንኛውም ክልል ሕገ መንግስቱን በመጣስ ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ የፌዴራሉ መንግስት ጣልቃ እንዲገባ የማዘዝ እና ሌሎች ከፍተኛ አገራዊ አንደምታ ያላቸው ሥልጣንና ኃላፊነቶች ተሰጥተውታል፡፡ ምክር ቤቱ ይህን የተቋቋመለትን ተልዕኮ እውን ለማድረግ የተለያዩ አደረጃጀቶችን በመፍጠርና የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት የሕዝቦችን እኩልነት፣ ፍትሓዊ ተጠቃሚነትና ዴሞክራሲያዊ አንድነት የሚያጎለብቱ ተግባራትን ከነውስንነቱም ቢሆን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

ሆኖም አገሪቱ ከያዘችው የለውጥ ጎዳና እንዲሁም አሁን እየቀረቡ ካሉ የሕዝብ ፍላጎቶችና ጥያቄዎች አንጻር ምክር ቤቱ በሕገ መንግስቱ የተሰጡትን ተልዕኮዎች በቀልጣፋ እና በውጤታማ አኳኋን ለመፈጸም በሚያስችለው ቁመና ላይ የሚገኝ አለመሆኑ በጥናቶች ተረጋግጧል፡፡ ምክር ቤቱን ለማጠናከር እና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር የወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 ሕግ ሆኖ ከወጣ ከ20 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ በመሆኑ በጊዜ እና በአተገባበር ሂደት ፈርጀ ብዙ ክፍተቶችና ችግሮች ተስተውለውበታል፡፡ የምክር ቤቱ ጽ/ቤትም ቢሆን ለተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ በሚመጥን አመራር፣ አደረጃጀትና አሰራር እንዲሁም በበቂና ብቃት ባለው የሠለጠነ የሰው ኃይል በመሙላት ረገድ የሚታየው ውስንነትም የዚሁ ችግር አካል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ስለሆነም የምክር ቤቱን ሕገመንግስታዊ ተግባርና ኃላፊነቱን፣ የሕግ ማዕቀፎችን፣ አደረጃጀቱን እና የአሰራር ስርዓቶችን በመፈተሽ ሁለንተናዊ የለውጥ ሂደት ውስጥ መግባት አስፈልጓል፡፡

## 2. የሕግ እና የአሠራር ሥርዓቶች ለማሻሻል የተሄደባቸው ሂደቶች

አገራዊ ለውጡን ተከትሎ የተቋም ግንባታ ለአገራዊ ግንባታ ያለውን አስፈላጊነት ግምት ውስጥ በማስገባት የምክር ቤቱን ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣንና ኃላፊነትን ማዕከል በማድረግ በአራት የትኩረት መስኮች በ (1) ብዝሃነት፣ ሕብረብሔራዊ አንድነትና ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ፣ (2) ሕገ መንግስት የበላይነት እና ሕገመንግስታዊነት፣ (3) ውጤታማ የፊሲካል ሽግግርና ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ማረጋገጥ፣ (4) ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ግንባታ በሚሉ ዘርፎች የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገ መንግሥቱ የተሰጡን ሥልጣንና ኃላፊነቶች አንጻር ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ በጥናቶቹ ግኝቶች ላይ ከባለድርሻ አካላት ማለትም የክልል ርዕሳነ መስተዳደሮች፣ ከክልል ምክር ቤቶች አፈጉባኤዎች፣ የፌዴራልና የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች፣

የኢፌዲሪ ጠቅላይ አቃቢ ሕግ፣ የሕገ መንግስት አጣሪ ጉባኤ አባላት፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመለከታቸው የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሁራን ያካተተ ሰፊ ውይይቶችን በማካሄድ ተጨማሪ አስተያየቶችንና ግብዓቶች እንዲካተቱበት ተደርጓል፡፡ በጥናቶቹ ግኝቶቹ እና የባለድርሻ አካላት ግብአቶችና አስተያየቶችን ወደ ሕግ እና የአሰራር ሥርዓት ማሻሻያ በመቀየር የአዋጅ ቁጥር 251/1993፣ አዋጅ ቁጥር 556/2005 እና የአባላት የስነምግባር ደንብ ቁጥር 1/1999 የማሻሻያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት ሕጎቹ ተሻሽለው ይወጡ ዘንድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲመሩ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

**3. የማሻሻያ አጠቃላይ አስፈላጊነት**

ነባሩ አዋጅ ቁጥር 251/1993 በስራ ላይ ከ20 ዓመት በላይ አስቆጥሯል፡፡ ይህም የፌዴሬሽን ምክር ቤት በጊዜ ሂደት በአፈጻጸም ትግበራ የሕግና የአሰራር ክፍተቶች በመፈጠራቸው ምክንያት የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሕገ መንግስታዊ መብቶች በተገቢው መንገድ ለማስከበር አዳጋች ያደረገው በመሆኑ፤

አገሪቱ ከያዘችው የለውጥ ጎዳና እንዲሁም አሁን እየቀረቡ ካሉ የሕዝብ ፍላጎቶችና ጥያቄዎች አንጻር ምክር ቤቱ በሕገ መንግሥቱ የተሰጡትን ተልዕኮዎች በቀልጣፋ እና በውጤታማ አኳኋን ለመፈጸም በሚያስችለው ቁመና ላይ የሚገኝ አለመሆኑ በጥናት የተረጋገጠ በመሆኑ፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤት አገራዊ ለውጡን ተከትሎ ሁለንተናዊ የለውጥ (ሪፎርም) ለማካሄድ በአራት የትኩረት መስኮች ማለትም (1) ብዝሃነት፣ ሕብረብሔራዊ አንድነትና ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ፣ (2) ሕገ መንግስት የበላይነት እና ሕገመንግስታዊነት፣ (3) ውጤታማ የፊስካል ሽግግርና ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ማረጋገጥ፣ (4) ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ግንባታ በሚሉ ዘርፎች የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገ መንግሥቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ኃላፊነቶች አንጻር ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ በጥናት ውጤቶቹ በተገኘው ግኝቶችና ምክረ ሃሳቦች መሰረት አሁን ያለውን የምክር ቤቱን የሕግ ማዕቀፎች፣ አደረጃጀት እና የአሰራር ስርዓቶችን ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ያመላክታሉ፡፡

ስለሆነም ምክር ቤቱን በሕገ መንግስቱ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም ምክር ቤቱን ለማጠናከርና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር በወጣው በአዋጅ ቁጥር 251/93 መሰረት በማድረግ ነባሮቹን የሕግ ማዕቀፎችን፣ የአሰራር ስርዓቶችን እና አደረጃጀቶችን በመፈተሽ እና ከሌሎች አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት እና መስተጋብር በመቃኘት ለሕብረብሔራዊ አንድነት ግንባታና ለዘላቂ ሰላም የድርሻውን ለመወጣት ያስችለው ዘንድ ሁለንተናዊ ተቋማዊ ለውጥ ለማካሄድ የጥናት ግኝቶችን ወደ ሕግ እና የአሰራር ሥርዓት ለመቀየር የሕግ ማዕቀፎቹን ማሻሻል አስፈልጓል፡፡

የምክር ቤቱን አሰራር ለብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚሰጠውን ምላሽ ቀልጣፋ እና ግልጽ ማድረግና ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በግልጽ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዋጁ መሻሻል ምክር ቤቱ በሕገ መንግሥት የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በተሟላ መንገድ እንዲፈጽም በማስቻል፣ ሕገ መንግሥታዊነትን፣ ዘላቂ ሰላምን ዋስትና ያለው ዲሞክራሲን ለማስፈን ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ፤ እነዚህን አጠቃላይ ጉዳዮች ለማሳካት ሕጉን ማሻሻል አስፈላጊ አድርጎታል፡፡

## 4. የተሻሻሉ ክፍሎች ዋና ዋና ጉዳዮች አጭር ማብራሪያ

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1) **አጭር ርዕስ**

በዚህ አንቀጽ ውስጥ በነባሩ አዋጅ ውስጥ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ለማጠናከርና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር ከሚለው ርዕስ ውስጥ *"ለማጠናከርና"* የሚለው ወጥቷል፡፡ እንዲሁም *"ተግባሩን"* የሚለውም "ተግባር" በሚል ተተክቷል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት አዋጁ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣንና ተግባሩን ከመዘርዘር ያለፈ አዲስ የሚያጠናክር ስልጣን ወይም ተግባር የሚሰጠው ስላልሆነ ቃሉ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

ስለሆነም የአዋጁ ስያሜ "የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመዘርዘር ተሻሽሎ የወጣ አዋጅ ቁጥር....../2013" ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ በሚል ተሻሽሏል፡፡

2) **ትርጓሜ**

በዚህ ክፍል በነባሩ አዋጅ ውስጥ ያልነበሩ አዳዲስ ቃላት ትርጓሜ ተሰጥቷቸው እንዲብራሩ ተደርጓል፡፡ ከእነዚህም መካከል "የከተማ አስተዳደሮች" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደር ናቸው፤ የሚል ተጨምሯል፡፡ ይህም ምክንያት ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በሕገ መንግስቱ የተቀመጠላቸውን ደረጃ ለመጠበቅ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ "ክልል" በሚለው ትርጓሜ ውስጥ አዲስ አበባ አበባ እና ድሬዳዋ አስተዳደርን እንዲወጣ ተደርጓል፤ ምክንያቱም የአሰራርና የግንኙነት ባህርይ የተለያየ በመሆኑ ክልል የሚለው ቃል በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 በተቀመጠው መሰረት መተርጎም አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ ሌላው አዲስ የተካተተው ትርጓሜ "ማሕበረሰብ" የሚል ቃል ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የሚያቀርቡት ሕገ መንግስታዊ የሙብት ጥያቄ እና "ማሕበረሰቦች" ማንነቴ ይታወቅልኝ ወይም ብሔርነት፣ ብሔረሰብነት ወይም ሕዝነበት እውቅና ይሰጠን ተብሎ ከሚቀርብ ጥያቄ የተለየ ከመሆኑም በላይ እነዚህን ሁለት ዓይነት ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚወሰዱ የአሰራር ሥርዓቶች፣ አግባቦች እና የሚሰጡ ምላሾች ፍጹም የተለያዩ በመሆናቸው በግልጽ ማስቀመጡ አስፈላጊ ነው፡፡

"አስተባባሪ ኮሚቴ"፣ "ጊዜያዊ ኮሚቴ"፣ "ቋሚ ኮሚቴ" ምንነት የተተረጎመበት ምክንያት በሌሎች የምክር ቤቱ የሕግ ማዕቀፎች ማለትም በጽሕፈት ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅና በምክር ቤቱ የአሰራርና የአባላት የሥነምግባር

ደንብ ቋሚ ኮሚቴዎችንም እንደሚጨምር ተደርጎ የተቀመጠ እና እስካሁንም ሲሰራበት የቆየ በመሆኑ እና በአዋጁ ውሥጥ የተጠቀሱ በመሆኑ መተርጎም አስፈለጊ ስለሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም "የመንግስት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ" እና "ሰው" የሚሉት ቃላት ወይም ሐረጎች በአዋጁ ውሥጥ የተጠቀሱ በመሆኑ ለአዋጁ ትግበራ መተርጎም አስፈለጊ ስለሆነ ነው፡፡

3) **የጾታ አገላለጽ**

የጾታ አገላለጽ በተመለከተ በነባሩ አዋጅ ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ በዚህ ረቂቅ ውስጥ በአንቀጽ 3 ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

4) **የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር**

በነባሩ አዋጅ አንቀጽ 3 የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር በሚለው ሥር ያልተካተቱ ሆኖም የምክር ቤቱ ሕገ መንግስታዊ ሥልጣንና ኃላፊነቶች የሆኑ በተለይ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመሆን በአንድ ክልል ሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱና ክልሉ ድርጊቱን ማስቆም ሳይችል ሲቀር ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ፣ ምክር ቤቱ ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሶስት አባላትን መርጦ እንደሚልክ፤ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 1162/2012 መሰረት ምክር ቤቱ የሕዝብ ብዛታቸው አነስተኛ በመሆኑ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተለየ ውክልና የሚያስፈልጋቸው ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነት እና ቁጥር የመወሰን ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በተሻሻለው ረቂቅ አዋጅ በአንቀፅ 4 ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

<u>**ክፍል ሁለት**</u>

<u>**ሕገ መንግስቱን ስለመተርጎም**</u>

በዚህ ክፍል በአንቀጽ 5 በመርህ ደረጃ ምክር ቤቱ ሕገ መንግስቱን ሲተረጉም ውጤቱ ምን እንደሚሆን፣ በአንቀጥ 6 የሕገ መንግስት ትርጉም ሊቀርብባቸው ስለሚችሉ ጉዳዮች፣ በአንቀጽ 8 ይግባኝ ስለማቅረቢያ የጊዜ ገደብ፣ በአንቀጽ 9 የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ማቅረብ ስለሚችሉ አካላት፣ በአንቀጽ 19 እግድን የሚመለከቱ በነባሩ አዋጅ ያልነበሩ እና በተለየ ሁኔታ ጉዳዮቹን አብራርተው የሚገልጹ ድንጋጌዎች ተቀምጠዋል፡፡ የእነዚህም ጠቀሜታ ምክር ቤቱ ሕገ መንግስቱን ሲተረጉም የሚያያቸው እና ለትርጉም የሚቀርቡ ጉዳች ምን እንደሆኑ፣ የትርጉም አቤቱታ የማቅረብ መብት ያላቸው እነማን እንደሆኑ፣ አቤቱታው በማን መቅረብ እንዳለበት የሚገልጹ ድንጋጌዎች መካታተቸው ለራሱ ለተርጓሚው ምክር ቤት አባላት እና ለዜጎች ግልጽነትን ይፈጥራል፡፡

ለምሳሌ በሕገመንግስቱንና በነባሩ አዋጅ ለትርጉም የሚቀርቡ ጉዳዮች በፍርድ ቤት ከተያዘ ጉዳይ ጋር ብቻ የተገናኙ እንደሆኑ ከመግለጻቸው ውጪ ሌሎች ሕገ መንግስታዊ ጉዳዮችና ክርክሮች ምን ምን አንደሆኑ በግልጽ አልተቀመጠም፡፡ ሆኖም በተግባር እንደተሚታየው ለትርጉም ቀርበው ምክር ቤቱ ውሳኔ

የሚሰጥባቸው ጉዳዮች በፍ/ቤት በተያዙ ጉዳዮች ብቻ አይደሉም፡፡ እነዚህ ከፍ/ቤት ውጪ የሚቀርቡ ጉዳዮች በፍርድ ሊወሰን በማይችል ማናቸውም ሕገ መንግስታዊ ጉዳይ ላይ በፌዴራል ወይም በክልል ሕግ አውጭ ምክር ቤቱ 1/3ኛ አባላት ወይም በፌዴራልም ሆነ በክልል አስፈጻሚ አካላት የሚቀርብ ጥያቄ እና በማናቸውም የመንግስት አካል ወይም የባለስልጣን የመጨረሻ ውሳኔ በሕገ መንግስቱ የተደነገጉት መሰረታዊ መብቶች እና ነጻነቶቹ ተጥሰዋል በሚል ማንኛውም ጥያቄ ለማቅረብ መብት ባለው ሰው የሚቀርብ አቤቱታ ነው፡፡

ይህ ረቂቅ ግን ከፍርድ ቤት ውጪ ከላይ የተመለከቱት ዓይነት የሚቀርቡ ትርጉም አቤቱታዎች መኖራቸውን፣ የትርጉም ጥያቄም በፍ/ቤት በተያዘ ጉዳይ በሚነሳ ሕገ መንግስታዊ ክርክር በፍ/ቤት ወይም በባለጉዳዩ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 2 ብቻ ሳይሆን ከፍ/ቤት ውጪም በሌሎች የመንግሥት አካላትም ለምሳሌ በፌዴራል እና የክልል ምክር ቤቶች፣ በአስፈጻሚ አካላት፣ በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉት መሰረታዊ መብቶች እና ነጻነቶቹ ተጥሰዋል በሚል ዜጎች መቅረብ እንደሚችሉ አብራርቶ ማስቀመጡ በተግባር ሥልጣኑን እና በአቤቱታ አቀራረብ ግልጽነትን ከመፍጠር አኳያ ጠቃሚ ነው፡፡ ሌላው ዜጎች የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ ሲያቀርቡ የሚከተሉት የአቀራረብ ስርዓት ስለሌለ በአቤቱታ አቀባበል እና ምርመራ ላይ በተግባር ችግር እየፈጠረ ያለ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረቂቅ ሕግ አቤቱታ አቀራረብን በተመለከተ እንዲወጣ መፍቀዱ እና መመላከቱ አሁንና ወደፊት በአቤቱታ አቀራረብ ላይ እየተፈጠሩ ያሉ እና የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት ይረዳል፡፡

በዚሁ ክፍል አዲስ ከተካተቱት ጉዳዮች መካከል አንዱ ይርጋን ይመለከታል፡፡ በሕገ መንግስቱ በይርጋ ቀሪ ከማይደረጉ ጉዳዮች እና የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እና ከመንግስት የሥልጣን ክፍፍል ጋር የተያያዙ ሕገ መንግሥታዊ ጥያቄዎች በስተቀር ሌሎች ክርክሮች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መብቶች ተጠይቀው መቋጨት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም የፍርድ ባለመብቶች በፍርድ ሂደት ያገኙቱን መብቶች በማረጋገጥ ክርክሮች አንድ ቦታ መቆም ያለበት ስለሆነ ነው፡፡ መብት አለኝ የሚል ተከራካሪም በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ጠይቆ እልባት ማግኘት ያለበት መሆኑንም የሚያመለክት ነው፡፡

በዚሁ ክፍል ሥር በአንቀጽ 11- 12 በተካተቱ አዳዲስ የረቂቁ ድንጋጌዎች ከሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው ጋር ምክር ቤቱ ስለሚኖረው የስራ ግንኙነት ማለትም የውሳኔ ሃሳብ ስለሚያቀርብበት ሁኔታ፣ የውሳኔ ሃሰብ ሲያቀርብ አስፈላጊ ከሆኑ ሰነዶች እና መረጃዎች ጋር አሟልቶ መሆን እንዳለበት፣ የአጣሪ ጉባኤው አባላት በማናቸውም ጉዳይ በሚመከተው ቋሚ ኮሚቴ ወይም በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባዔ በማናቸውም ሕገ መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ሲጠየቁ ማብራሪያ መስጠት እንዳለባቸው የሚገልጹ ድንጋጌዎች ስራን ከማቀላጠፍ እና ቀጥተኛ ሕጋዊ ግንኙነትን ከመፍጠር አንጻር ጠቃሚ ናቸው፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች በተግባር እየታዩ ያሉ ችግሮችን ለምሳሌ ከጉባኤው የሕገ መንግስት ትርጉም የውሳኔ ሃሳብ ሲቀርብ ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር ባለመሆኑ የመጻጻፍ ሁኔታ እና የስራ መዘግየት እየታየ ስለሆነ በተጨማሪም የጉባዔው አባላት በቋሚ ኮሚቴ ወይም በም/ቤቱ ጉባዔ ቀርበው እንዲያስረዱ ሲጠየቁ አልፎ አልፎ የሚታየውን የአሰራር ችግር ሕጋዊ መሰረት በማስያዝ እነዚህ ድንጋጌዎቹ ይቀርፋሉ፡፡ የሕገመንግስት አጣሪ

ጉባኤው ለም/ቤቱ በየጊዜው የስራ ክንውኑ ሪፖርት የማቅረብ ሁኔታም በተመሳሳይ ም/ቤቱ ስለጉባኤው ሥራ በየወቅቱ እንዲያውቅ እና ክትትል እንዲያደርግ ይረዳዋል፡፡ ሌላው ከዚህ ጋር የተያያዘ የሕገመንግስት አጣሪ ጉባኤ ለም/ቤቱ የሚያቀርበው ምክረ ሃሳብ የትርጉም የውሳኔ ሃሳብ እንጂ የመጨረሻ ውሳኔ ስላልሆነ ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ያልሰጠበት ወይም እየታየ ያለ ጉዳይ ስለሆነ ጉዳዩን በማንኛውም የመገናኛ ብዙሃን መልቀቅ ወይም በጆርናል መልክ መታተም የለበትም በሚል ማካተት አስፈልጓል፡፡

ሌላው በዚህ ክፍል በአንቀጽ 15 እና 16 ስለማስረጃ አሰባሰብ እና የውሳኔ አሰጥጥ ሂደት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች አሉ፡፡ ም/ቤቱ በሕገ መንግሥት ትርጉም ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ከሚመለከታቸው አካላት ማስረጃዎች ወይም አስተያየቶች እንዲቀርቡ ትዕዛዝ የሚሰጥበትና አስፈላጊ የሚሆንበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ ለምክር ቤቱ የቀረበ የህገ መንግስት ትርጉም ጉዳይ ሰፋ ያለ የህዝብን ጥቅም የሚመለከት ወይም መሰረታዊ የግል ወይም የጋራ መብቶችን የሚመለከት በሚሆንበት ጊዜ የምክር ቤቱ አጋር (amicus curiae) አመልካች በመሆን በግራ ቀኙ ክርክር ለማቅረብ የሚጠይቁ ተቋማትን ወይም ባለሞያዎችን ሊያስተናግድ በመጋበዝ ጉዳዩን እንዲያስረዱ ሊያደርግ እንደሚችል ተመላክቷል፡፡ ይህም ምክር ቤቱ የምክር ቤቱ ሕገ መንግስታዊ ውሳኔዎችን ለመስጠት በበቂ እውቀት እና መረጃ ላይ በመመስረት ውሳኔዎችን ለመስጠት አስቻይ ስለሚያደርገው ነው፡፡ ሌላው ለውሳኔ አሰጣጥ ጠቃሚ ስለሆኑ እንዲህ ዓይነት ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ ወይም በአካል ቀርቦ እንዲያስረዳ ም/ቤቱ የታዘዘ አካል የታዘዘውን መፈጸም እንዳለበት፣ ይህን የማያደርግ ከሆነ አግባብ ባለው ሕግ እና ሥርዓት ተጠያቂ እንዲሆን የሚያደርጉ አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች መኖራቸው የም/ቤቱን ሥራ እና የውሳኔ አሰጣጥ ከማሳለጥ አንጻር ጠቃሚነቱ የጎላ እንደሚሆን ታምኖበት ነው፡፡

ከዚሁ ጋር የረቂቁ አንቀጽ 18 በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ሕጎችን፣ ተሞክሮዎችን በመቀመር በጥናት በመለየት ለም/ቤቱ የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ የተደነገገው የኮሚቴውን ኃላፊነት ከፍ በማድረግ የም/ቤቱን የውሳኔ አሰጣጥ ጥራት እና ጥልቀት ለማሳደግ የሚረዳ ነው፡፡ በዚህ ቦታ ሌላው ጉዳይ በነባሩ ሕግ የሚመለከተው ኮሚቴ በይግባኝ ምክር ቤቱ የሚቀርቡ የትርጉም አቤቱታዎችን ምርመራ በተመለከተ ለም/ቤቱ አጠቃላይ ጉባዔ መቅረብ ይገባዋል ወይም አይገባውም በማለት አንዲወስን ውክልና ሊሰጠው ይችላል፤ የሚለው ነባር ድንጋጌ የዜጎችን የመሰማት መብት የሚያጠብብ ስለሆነ እንዲወጣ መደረጉ መጠቀስ አለበት፡፡

በዚህ ክፍል በአንቀጽ 19 ጉዳዮችን ባሉበት ደረጃ ስለማቆየት ወይም ስለእግድ የተመለከተው አዲስ ድንጋጌ ነው፡፡ ም/ቤቱ የሚያያቸው የትርጉም ጉዳዮች በምርመራ ላይ ሆነው በተለይ በፍ/ቤት ታይተው የመጡ ጉዳዮች ከውሳኔ በፊት ቢፈጸሙ ውሳኔው ዋጋ እንዳያጣ፤ ጉዳዩን አግዶ ማቆየት በጣም አስፈላጊ ሲሆንና አቤቱታ አቅራቢዎች ሲጠይቁ የሚታገድበት አግባብ ተመላክቷል፡፡ ይህ በነባሩ ሕግ ያልነበረ ነው፡፡ በተግባር እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎች በቀርቡም በአሁኑ ወቅት ጉዳዮችን ባሉበት ለማቆየት የሚያስችል የሕግ ድንጋጌ ባለመኖሩ እና የአሰራር ችግር ሆኖ በመታየቱ ይህን ክፍተት ለመሙላት እንዲያስችል ታስቦ የተቀመጠ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በተመሳሳይ የአጣሪ ጉባኤው አዋጅ ሲሻሻልም የተካተተ ጉዳይ ነው፡፡

ሌላው በረቂቁ አንቀጽ 22 የሕገ መንግስት ትርጉም ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ በውሳኔው መሰረት እንዲፈጸም በሕግ በተወሰነ ጊዜ የገደብ ለሚመለከተው ባለጉዳይ ወይም የመንግሥት አካል ውሳኔውን ለማሳወቅ የሚያስችል የተቀመጠው አዲስ ድንጋጌም ቀልጣፋ አገልግሎትንና ተጠያቂነትን የማስፈን ዓላማ ያለው ነው፡፡ የሕገ መንግስት ትርጉም ውሳኔ ደረጃውን በተመለከተ የመጨረሻ እና አስገዳጅ ከመሆኑ በላይ የውሳኔው ደረጃ የሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ ክብደት ያለው መሆኑን በአዲሱ ረቂቅ አዋጅ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ይህም የሕገ መንግስት ትርጉም ሕገ መንግስታዊ አነቀጾችን በመተርጎም የሚሰጥ ውሳኔ ስለሆነ የሕገ መንግስት አካል ተደርገው ስለሚቆጠሩ ነው፡፡

በመጨረሻም የሕገ መንግስት ትርጉም ውሳኔዎችን በፌደራሉ ቋንቋ፣ በክልል የስራ ቋንቋች እና በእንግሊዝኛ እንዲታተም እና ለሁሉም አካላት ተደራሽ እንዲሆን ለማድረግ ይረዳ ዘንድ የተካተተ አዲስ አንቀጽ ነው፡፡ ይህም ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሚገባቸው ቋንቋ ሕገ መንግስታዊ የትርጉም ውሳኔዎች እንዲረዱ እና ጥቅም ላይ እንዲያውሉት ቢያንስ በክልል የሥራ ቋንቋዎች ማሳተም ተደራሽነቱን ያረጋግጣል፡፡ ይህም ምክር ቤቱ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሚወከሉበት በመሆን ብዝሃነትን ባማከለ ሁኔታ ሥራዎቹን ማከናወን ለሕብረ ብሔራዊ አንድነት መጎልበት ያለው አስተዋጽኦ በመሆኑ ነው፡፡

## ክፍል ሦስት

## የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን በተመለከተ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ እና ስለመወሰን

ይሕ ክፍል የያዛቸው ድንጋጌዎች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን አስመልክቶ የሚነሱ ጥያቄዎችን ስለማስተናገድ እና ስለመወሰን የተመለከቱ ናቸው፡፡ በዋናነት በዚህ ክፍል ስር በአንቀጽ 24 ንኡስ ቁጥር (2) እና (3) የተመለከተው በነባሩ ሕግ በጥቅሉ ማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የሚያቀርባቸውን የማንነት እና ሌሎች ጥያቄዎች ለሁለት በመለየት የማንነት ጥያቄ የሚያቀርበው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39 መሰረት ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብነቱ ያልታወቀለት ማሕበረሰብ እንደሆነ ጥያቄው በአንቀጥ 39(5) በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ምላሽ የሚሰጣቸው መሆንን የሚያመላክት ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብነቱ ታውቆ ነገር ግን ሌሎች በቋንቋ የመጠቀም፣ ባህል የማሳደግ፣ ሚዛናዊ ውክልና መብቶችን የሚመለከቱ አቤቱታዎች የሚያቀርበው በማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ እንደሆነ የጥያቄዎቹን ፈርጅ በመለየት ሳይደበላለቅ ለማስቀመጥ የተሞከረበት አግባብ የማሻሻያው ማሳያ ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በነባሩ ሕግ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ጋር ተያይዞ ጥያቄ ከቀረበ በኋላ ም/ቤቱ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ይወስናል፤ በሚል የሚደነግግ ሲሆኑ ከዚህ ውጪ አቤቱታ ከቀረበ በኋላ እና ከውሳኔ በፊት ም/ቤቱ ምን ምን ተግባራትን ያከናውናል በሚለው ጉዳይ ላይ ምንም የተገለጸ ነገር የለም፡፡ ሆኖም ከውሳኔ በፊት ጥናት የማድረግ፣ ሕዝብን ፍላጎት የመጠየቅ የመሳሰሉት ቁልፍ ተግባራት በግልጽ እና ዘርዘር ተደርገው በአዲሱ ረቂቅ በአንቀጽ 29 እና 30 ላይ መቀመጣቸው ም/ቤቱ እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች ሲቀርቡለት በግልጽ በመረዳት ሕጋዊ ሂደቱን ተከትሎ አቅጣጫ እንዲሰጥ፣ የሚመለከተው ኮሚቴ እና ባለሙያዎችም ይህንኑ

ግልጽ የሕግ ድንጋጌ ተከትለው በጥናት እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ሥራ እንዲሰሩ የሚያስችል በመሆኑ ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ ያለውን የአሰራር ክፍተት የሚሞላ ነው፡፡

በረቂቁ አንቀጽ 32 ውሳኔ አሰጣጥ ላይ እንዲሁ እንደጥያቄዎች ዓይነት ውሳኔ ስለሚሰጥበት አግባብ፣ ስለአፈጻጸም ክትትሉ ዘርዘር ተደርገው የተቀመጡ ድንገጋዎችም ም/ቤቱ ኃላፊነቱን በተሟላ መንገድ ከመወጣት አንጻር የሚያግዙ ናቸው፡፡ ሌላው በአንቀጽ 31 የተቀመጠው አዲስ ድንጋጌ በአንድ ክልል የቀረበ የማንነት ጥያቄ ታይቶ ክልሉ ጥያቄው ተገቢ አይደለም በሚል ውሳኔ ከሰጠበት በኋላ ውሳኔውን የሚያስለውጡ ሁኔታዎች ቢፈጠሩና በድጋሚ አይቶ የተለየ ውሳኔ ለመስጠት ቢወስን ለዚሁ አሰራር ቦታ የሚሰጥ ሆኖ ተቀርጿል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ጥቄው ለፌ/ም/ቤት ቀርቦ በመታየት ላይ እያለ ከላይ በተመከተው አግባብ ክልሉ አቤታውን በድጋሚ አይቶ ቢወስን ም/ቤቱ ጉዳዩን የሚያስተናግድበት እና ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ ምን እንደሚሆን በግልጽ ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ አካሄድ እንደ አዲስ በረቂቁ አንቀጽ 32 እንዲቀመጥ የተደረገ ሲሆን በተግባርም እየተሰራበት ያለ አካሄድ ነው፡፡

## ክፍል አራት

## አለመግባባቶች ስለመፍታት

ይህ ክፍል አለመግባባቶችን መፍታት የሚመለከት ሲሆን በዋናነት በተግባር ላይ ያሉ ችግሮችን ይቀርፋሉ ተብለው የሚታሰቡ በነባሩ ሕግ የሌሉና በረቂቁ የተካተቱ ሁለት ጉዳዮች ናቸው፡፡ በነባሩ አዋጅ በክልሎች መካከል ወይም በፌዴራል እና በክልል መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በሁለቱ ወገኖች በውይይት እንዲፈታ ምክር ቤቱ ሁኔታዎች እንደሚያመቻች ከመቀመጡም በላይ ሁለቱ ወገኖች ካልተስማሙ በአንድ ወይም በሁለቱም ወገኖች በሚቀርብ ጥያቄ ምክር ቤቱ በሕገ መንግስቱ መሰረት ለጉዳዩ እልባት እንደሚሰጥ ተቀምጧል፡፡ ይሁን እንጂ በተግባርም እንደታየው በሁለት ወገኖች መካከል የሚያወዛግብ ጉዳይ እንዳለ እየታወቀ አንዱ ወይም ሁለቱም ወገኖች ጥያቄ ባለመቅረባቸው ምክንያት ብቻ ምክር ቤቱ የመፍትሔ እርምጃ ሳይወሰድ ቆይቷል፡፡ ይህንን ክፍተት ለመሙላት አንዱ ወይም ሁለቱ ወገኖች የፌዴሬሽን ምክር ቤት መፍትሔ ካልጠየቁ እና ችግሩ ከቀጠለ ምክር ቤቱ በራሱ አነሳሽነት መፍትሔ እንዲያፈላልግ የሚፈቅድ አሰራር በአዲሱ አዋጅ ተካቷል፡፡ ሌላው  በአንቀጥ 41 ላይ የተቀመጠው የአስተዳደር ወሰን ማካለልን የተመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ የአስተዳደር ወሰን አለመግባባት ሲፈጠር በሕዝበ ውሳኔ የሕዝቡን ፍላጎት የማረጋገጥ እና የመወሰን ተግባር እንደሚከናወን በነባሩ ሕገም የተደነገገ ነው፡፡ ሆኖም ከሕዝብ ውሳኔም በኋላ በምን ያህል ጊዜ የሕዝቡን ፍላጎት ተከትሎ ወሰን እንደሚካለል እና በማካለሉ ሂደት በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የመንግስት አካላት እና ክልሎች ያላቸው ኃላፊነት በግልጽ አለመመልከቱ በተግባር ሕዝበ ውሳኔ በተደረገባቸው አካባቢዎች ከሕዝበ ውሳኔ በኋላ የሚታዩ ችግሮች እና ግጭቶች የክፍተቱ ማሳያ ናቸው፡፡

የሕዝበ ውሳኔ ውጤት ከታወቀ በኋላ የወሰን ማካለሉ ተግባር በ6 ወር ጊዜ መከናወን አለበት የተባለበት ምክንያት አንደኛ በወሰን ማካለሉ ሂደት የሚሳተፉ ክልሎች እና አካላት ለማካለሉ በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉ፤ ሁለተኛ ከዚህም ከረዘመ አለመግባባቶችና ግጭቶች ሊከሰቱ ስለሚችሉ ይህንን ለማስወገድ ታስቦ ነው፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ሕዝበ ውሳኔ ከተካሄደ እና ወሰን ከተካለለም በኋላ የሰላም ግንባታ፣ የልማት እና የሕዝቦች የእርስበርስ ግንኙነት የማዳበር ስራዎች መሰራት እንደሚኖርባቸው በረቂቁ አንቀጽ 42 አዲስ ድንጋጌ ሆኖ መግባቱ ለግጭት መከላከል እና ለሰላም ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

## ክፍል አምሥት

## ስለ ድጎማ እና የጋራ ገቢዎች ቀመር አወሳሰን

ይህ ክፍል ድጎማ እና የጋራ ገቢዎች ቀመር አወሳሰን የሚለከት ሲሆን በዚህ ክፍል ሥር ነዋናነት በነባሩ ሕግ ያልነበሩ አዳዲስ ድንጋጌዎች ተካትተዋል፡፡ እነዚህም በአንቀጽ 51፣52፣53 የተመለከቱ ናቸው፡፡ እነዚህም ድንጋጌዎች ያስፈለጉበት ምክንያት የድጎማና የጋራ ገቢዎች ማከፋፈያ ቀመር ሲዘጋጅና ሲወሰን ም/ቤቱ ሊያሳካቸው የሚገቡ ዓላመዎችና ሊከተላቸው የሚያስፈልጉ መርሆዎችን በግልጽ ማስቀመጥ ለዜጎች ሕገ መንግስታዊ የመልማት ሙብት ለፌዴራል መንግስት ለክልሎች ትብብር እና ግንኙነት መዳበር፣ ለክልሎች የተመጣጠነ እድገት እንዲሁም ዲሞክራሲያዊ አንድነትን ለማጠናከር በሚሰሩ ስራዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ ስለሚኖራቸወ ነው፡፡

## ክፍል ስድስት

## በሕዝቦች መካከል እኩልነትና አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር ስለማድረግ

ይህ ክፍል በሕገ መንግሥቱ የተደነገገው የሕዝቦች እኩልነትና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር የሚደርጉ ድንጋጌዎችን የያዘ ነው፡፡ ይህንን የተመለከቱ ድንጋጌዎች በነባሩ አዋጅ በጥቅል የተመላከቱ በመሆናቸው ለአፈጻጸም አስቸጋሪ መሆናቸው በተግባር እየታየ ያለ ጉዳይ ነው፡፡ በአዲሱ ረቂቅ ላይ ግን ችግሮቹን ለመቅረፍ ዘርዘር ያሉ የምክር ቤቱ እና ባለድርሻ አካላት ሚና የሚለዩ የሕግ እና አሰራር ስርዓቶች ተቀምጠዋል፡፡ እዚህ ጋር መጠቀስ ያለበት የመሰረተ ልማት ሥርጭት ፍትሃዊነት ማረጋገጥ በተመለከተ በአንቀጽ 54 በንዑሳን አንቀጽ ከ 1 እስከ 9 የተመላከቱትን በዝርዝር እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

ይህም ምክር ቤቱ የፌዴራል የመሰረተ ልማት አውታሮች ሥርጭት ፍትሐዊነት የሚለካው አስቀድሞ በተለዩ መስፈርቶችና መግባባት በተደረሰባቸው መለኪያዎች መሰረት መሆኑን፤ የሚመለከታቸው ተቋማት የመሰረተ ልማት ሥርጭት ፍትሐዊነትን አስመልክቶ የአፈጻጸም ሪፖርት ለምክር ቤቱ እንደሚያቀርቡ፤ ምክር ቤቱም ክልላዊ የመሰረተ ልማት ስርጭቶችን በየጊዜው በመከታተል ወቅታዊ ግብረመልስ ለሚመለከተው ተቋም እንደሚሰጥ፤ ምክር ቤቱ በክልሎች የፌዴራል የመሰረተ ልማት አውታሮች ሥርጭት

ፍትሐዊነት የጎደለው መሆኑን ሲያምን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና ለሚመለከታቸው ተቋማት እንደሚያሳውቅ፤ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ለተቋማቱ በተሰጠው አስተያየትና ግብረመልስ የማስተካከያ እርምጃዎች ስለመወሰዳቸው እንደሚከታተልና ፍሃዊነትን በጋራ እንደሚያረጋግጡ ተቀምጧል፡፡

የሕዝቦችን እኩልነት እና አንድነትን ለማዳበር የሚያግዙ እርምጃዎች በአንቀጽ 55 ላይ ከነባሩ አዋጅ በተጨማሪ በአዲስ መልክ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ከነዚህም መካከል በአገራዊ ማንነት እና በብሔር ማንነት መካከል ሚዛን ለመጠበቅ የሚያስችሉ እርምጃዎችን የመውሰድ፤ ለአገራዊ አንድነት በሚጠቅም መልኩ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በፌዴራል ተቋማት ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና እንዲኖራቸው የመስራት፤ ልሳነ ብዝሃነት እንዲዳብር የሚያስችሉ እርምጃዎችን የመውሰድ እና አካታች የሆነ የፌደራል የፖለቲካ ባህል እንዲዳብር የሚያስችሉ እርምጃዎችን እንደሚወሰድ በረቂቁ በአዲስ መልክ ተካቷል፡፡ እነዚህ የተካተቱበት ምክንያት ምክር ቤቱ የሕዝቦች እኩልነትና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር ለማድረግ የሚያስችል መሆናቸው በጥናት በመረጋገጡ ነው፡፡ እንደዚሁም ምክር ቤቱ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የተወከሉበት በመሆኑ ልሳነ ብዝሃነትን ማዳበር ለሕብረ ብሔራዊ አንድነት ማዳበር ከፍተኛ ሚና ያለው ከነመሆኑም በላይ ተልእኮውን ለማሳካት፣ ለማስረጽ እና ለማስተማር ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዘቦች በሚገባቸው ቋንቋ መጠቀም ከላይ የተጠቀሰውን ተልዕኮ ለማሳካት አስፈላጊነቱ የጎላ ያደርገዋል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን ስለመለየት

በዚህ ክፍል ምክር ቤቱ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸውን የፍትሐብሔር ጉዳዮች የመለየት ስልጣኑን አስመልክቶ አዳዲስ ነጥቦች በአዲስ መልክ ተካተዋል፡፡ የፍትሐብሔር ሃሳን ማመንጨት በተመለከተ የፌዴሬሽን ምክር ቤትና የክልሎች የጋራ ምክክር መድረክ የፍትሐብሔር ጉዳይ ሃሳቦችን ሊያመነጭ እንደሚችል ተመላክቷል፡፡ በነባሩ አዋጅ ከነበረው የፍትሃብሔር አምንጪዎች በተጨማሪ አንድ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ባልተጣጣመ ሁኔታ እየተተገበረ ያለ ከሆነ ወይም የጉዳዩ በየክልሉ የተለያየ የአፈጻጸም ተሞክሮ አንድ የጋራ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመፍጠር እንቅፋት የሚሆን ከሆነ ወይም ጉዳዩ ከአንድ በላይ ክልሎችን በጋራ የሚመለከት ከሆነ ምክር ቤቱ ይህ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ እንዲወጣለት ሊያደርግ እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ በተጨማሪም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተለይቶ የቀረበለትን የፍትሐ ብሔር ጉዳይ በተቻለ ፍጥነት ሕግ ሆኖ ማውጣት እንዳለበት በአዲሱ ረቂቅ ተካቷል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ስለምርጫ ክልል አከላለል እና ስለ ልዩ ውክልና

በዚህ ክፍል ከምርጫ ክልሎች አከላል ጋር ተያይዞ ያለው ጉዳይ በነባሩ አዋጅ ም/ቤቱ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የምርጫ አከላልን አስመልክቶ የሚቀርብለትን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ እንደሚያጸድቅ የተመለከተ ቢሆንም ምርጫ ቦርድ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ እንዳለበት የተገለጸ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም ግዴታን ከመወጣትና ተጠያቂነትን ከማስፈን አንጻር በተግባርም ምርጫ ቦርድ በሕጉ መሰረት የውሳኔ ሃሳብ በተገቢው ጊዜ የሚያቀርብበት ሁኔታ ስለማይታይ በረቂቅ አንቀጥ 62 ንዑስ ቁጥር 2 የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አጠቃላይ አገራዊ ምርጫ ከመካሄዱ ከአንድ ዓመት በፊት የምርጫ ክልሎችን አከላለል ረቂቅ ለምክር ቤቱ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ እንዳለበት ግዴታ የሚጥል የሕግ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ምክር ቤቱም የቀረበለትን የምርጫ ክልሎችን አከላለል ረቂቅን በምን መስፈርቶች በመመርመር ማጽደቅ እንዳለበት ተቀምጧል፡፡

በዚህ ክፍል በአዲስ መልክ በረቂቁ ከተካተቱት መካከል አንዱ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የልዩ ውክልን የሚመለከተው ይገኝበታል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1162/2012 መሰረት ምክር ቤቱ የሕዝብ ብዛታቸው አነስተኛ በመሆኑ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተለየ ውክልና የሚያስፈልጋቸው ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነት እና ቁጥር የመወሰን ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የተደነገገ በመሆኑ እና ይህንን የሚመለከት አንቀጽ ለማካተት ተሞክሯል፡፡

## ክፍል አሥር

## ስለኮሚቴዎች

ይህ ክፍል ስለ ም/ቤቱ ኮሚቴዎች አደረጃጀት ሥልጣንና ተግባር የሚዘረዝር ሲሆን በነባሩ ሕግ ያልነበረ በረቂቁ እንዲገባ የተደረገው ስለኮሞቴዎች አጠቃላይ ሥልጣንና ተግባር የሚመለከት ድንጋጌ ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ አስፈላጊነት ኮሚቴዎች በም/ቤቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ወሳኝ ሚና ያላቸው ስለሆነ አጠቃላይ ሥልጣንና ተግባራቸውን በግልጽ መደንገጉ ኃላፊነትና ተጠያቂነትን አጣምሮ ውጤታማ ሥራ ከመሥራት እና ተልዕኮን ከመወጣት አንጻር የራሱ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው ነው፡፡